የሰ/መ/ቁ. 25588

የካቲት 6 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** መርየን ሃሰን ዑመር - ቀረበች

**ተጠሪ፡-** መውሊድ ተኸል እስማን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት የግልና የጋራ ሀብትን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ተጠሪው የወሰደብኝን የግሌ የሆነውን አንድ ክፍል ቤት፣ ቀደም ሲል የሰጠሁትን 96 ፍየሎች እና በመካከላችን አለመግባባት ከመፈጠሩ በፊት ከቤቴ ውስጥ አስቀምጬው የወሰደብኝን ብር 5900 ይመልስልኝ በማለት በሶማሌ ክልል ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካችና ተጠሪ በትዳር ተሳስረን የቆየን ቢሆንም የየግላችን የሆነ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የለንም፣ ስለተባሉት ፍየሎችና ስለገንዘቡ አንድም የማውቀው ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ሕጋዊ የትዳር ትስስር እንዳላቸው ገልፆ በክሱ ላይ የተጠቀሰው አንድ ክፍል ቤት የአሁን አመልካች የግል ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፣ 96ቱን ፍየሎች አመልካች ለተጠሪ የሰጧቸው መሆኑን በምስክሮች አስረድተዋል፣ ብር 5900 ተጠሪ ከአመልካች መውሰዳቸው ግን አልተረጋገጠም በማለት ወስኗል፡፡



የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ለሸሪአ ፍ/ቤት ነው፣ ቤቱን የሠራሁት እኔ መሆኔን በምስክሮች አረጋግጫለሁ፣ ካርታውንም በአመልካች ስም እንዲመዘገብ ያደረግኩት በቅን ልቦና መሆኑን እያረጋገጥኩ ፍ/ቤቱ አይገባህም ሲል የወሰነብኝ ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም ከተጠሪ ጋር በትዳር ተሳስረን ስንኖር በጋራ ያፈራነው አንድም ንብረት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና እና ይግባኙ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ቤቱ የተሠራው አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑ በምስክሮች ስለተረጋገጠ ካርታው በአመልካች ስም መመዝገቡ ብቻ ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን እያረጋግጥም ስለዚህ ቤቱ የሁለቱ የጋራ ሀብት ነው፣ ፍየሎቹን አመልካች ለተጠሪ ሠርቶ እንዲጠቀም ብለው የሰጧቸው መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካችም ክዶ ስላልተከራከረ እንዳመነ ተቆጥሮ የፍየሎቹን ዋጋ ብር 14400 /አሥራ አራት ሺህ አራት መቶ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡

የአሁን ተጠሪ በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ ንብረቶቹን ያፈራነው በጋራ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የፍየሎቹን ዋጋ ተጠሪ ይክፈል በማለት የወሰነው ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን የገለፁ ሲሆን አመልካችም የስር ክርክራቸውን በመድገም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ችሎቱ በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ፀንቷል በማለት ወሰነ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን ተጠሪ ለሰበር ችሎቱ በድጋሚ አቤቱታ በማቅረባቸው ችሎቱ ጉዳዩን በሌላ ጊዜ በድጋሚ በማየት በዚያው መዝገብ በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ችሎቱ በሁለተኛው ውሣኔ የስር ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ የቤተሰብ ጉዳይ መሆኑን ሲገነዘቡ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባቸው ይህንን አላደረጉም፣ የሰበር ችሎቱም በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን ይህንን ስህተት

ባለማጤን በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፣ ስለዚህ ጉዳዩ ወደ ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም የአሁን አመልካች በሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የክልሉ ሰበር ችሎት ለሁለተኛ ጊዜ በሰጠው ውሣኔ በፍርድ ሊወሰን የሚችልን ማንኛውምንም ጉዳይ ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብቴን በሚጥስ መልኩ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት ሊታይ ይገባል በማለት የወሰነ ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አጽድቄዋለሁ ያለውን ውሣኔ በሌላ ቀን ችሎት ሽሬዋለሁና ክርክሩ በሸሪአ ፍ/ቤት ይታይ ብሎ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የክልሉ ሰበር ችሎት በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ራሱ ደግሞ በማየት በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት አንድ ጊዜ አይቶ ውሣኔ ያሳረፈበትን ጉዳይ በድጋሚ ሊያይም ሆነ ሊወስን በመርሕ ደረጃ የማይችል ሲሆን ነገር ግን በሕግ ላይ በተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ በድጋሚ ጉዳዩን ሊመለከተው ይችላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ጉዳዩ በድጋሚ ይታይልኝ ብለው ስላመለከቱ ብቻ ጉዳዩን እንደገና አይቶ ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ስህተት ነው ብለናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>



1. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ M/G/14/98 በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ ሰበር ሰሚ ችሎ 206 ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 05/1/210/97 ዓ.ም. በኅዳር 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ